# ኢዴፓ በዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ ታወቀ

የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) ከምርጫ 97 በኂላ ከቅንጅት ተለይቶ የራሱን አቋም በማራመዱ ምክንያት ቀደም ሲል የነበረው ተቀባይነት ተሸርሽሮ እንደነበርና ባለፉት ዓመታት በአቋሙ ጸንቶ ሃሳቡን ለሌሎች ለማስረዳት በመቻሉ፤ በሕዝቡም ሆነ በዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እየተሻሻለ መምጣቱን ከተለያዩ ምንጮች ያሰባሰብናቸው መረጃዎች አመለከቱ።

ተቀማጭነታቸው አዲስ አበበባ የሆኑ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት ባለፉት ዓመታት ከኢዴፓ ይልቅ "ግዙፍ ናቸው" ለተባሉ ፓርቲዎች ቅድሚያ ይሰጡ እንደነበር ለእነዚህ ወገኖች ቅርበት ያላቸው ምንጮች አመልክተው፣ ይሁን እንጂ ኢዴፓ ያለምንም መዋለል በያዘው አቋም ፀንቶና ለሕዝቡ መብትና ጥቅም ቅድሚያ ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ጥያቄዎቹ ሁሉ ተገቢ ምላሽ እንዲያገኙ ባሳየው ትጋት በዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍ ያለ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን ገልጸዋል።

ኢዴፓ በዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ዘንድ "በተጨባጭ እውነታ ላይ የተመሰረተ (Pragmatic) የተግባር ፓርቲ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸውን እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልጸዋል። "ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው የአውሮጳ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ከሌሎች ፓርቲዎች አስቀድመው የኢዴፓን አመራር ማነጋገራቸው ነው" ሲሉ እነዚሁ የዜና ምንጮች ጨምረው ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና፣ ራሱን ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የበላይ አድርጎና አግዝፎ የሚመለከተው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ሐሙስ ዕለት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ በተለይም በአፍሪካ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ላይ እምነት የሌለው መሆኑንና የአውሮጳ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን አባላትም እስከ አሁን ድረስ እንዳላነጋገሩት ማማረሩን የአገር ውስጥ ጋዜጦች ዘግበዋል።

በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የመድረክ የወቅቱ ሊቀ መንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ "የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ የሚባለው የለጋሽ ሀገራት ስብስብ እስከ አሁን ምንም የፈየደው ነገር የለም። ከዚህም በኂላ ምንም አንጠብቅም" ማለታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመልክቷል።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡን ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ታዛቢዎች "ዶ/ር በየነ እንዲህ ዓይነት የመረረ አቋማቸውን ማንጸባረቃቸው የዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ ለኢዴፓ ቅድሚያ በመስጠቱ ተበሳጭተው ሊሆን ይችላል" የሚል ግምታቸውን ተናግረዋል። "ይሁን እንጂ" ይላሉ እነዚሁ አስተያየት ሰጪዎች "ይሁን እንጂ የዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ መድረክን ተወት እያደረገው የመጣው ከዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት ስርዓት ውጭ እያሳያቸው በመጣው ባህሪያት ምክንያት ነው" ይላሉ።

ይህንን አባባላቸውን ሲያብራሩም፤ “መድረክ ገና የምስረታ ሂደቱን ሳያጠናቅቅ የኢዴፓ አመራር በተገኘበት አልነጋገርም አለ፡፡ ቀጥሎ ከገዥው ፓርቲ ጋር ድርድር እንዲያደርግ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲቀርብለት አሳማኝ ያልሆኑና ከዲፕሎማሲያዊ ማዕቀፍ ውጭ የሆኑ ምክንያቶችን በመደርደር ግትር አቋም ይዞ አፈነገጠ፡፡ ከዚያም ወዲህ ቢሆን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ምሬትን ከማሰማት ውጭ ለሀገሪቱ ፖለቲካ የሚበጅ ገንቢ ሚና ሲጫወት አልታየም፡፡ በእነዚህና በሌሎችም ለዲፕሎማሲያዊ አሰራር የማይመቹ አቀራረቦች የዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ ተማሯል፡፡ ይህንንም ምሬቱን መድረክን በማግለል በተግባር አሳይቷል” በማለት አብራርተዋል፡፡